# ገሞራው

## ከመስፍን ጉግል

እድለኛስ  ነበረ ፣ ገሞራው ሲፈጠር፤
በኪነ ጥበቡ ፣ ተንቆጥቁጦ ሲኖር፤
እሱ ግን ጀግና ነው ፣ ስጦታውን ንቆ፤
አሳልፎ ሰጠ ፣ ሕይወቱን አውልቆ፤
አንዴ ሳይኖራትም ፣ በፈቃዱ ገሎ፤
ለተገፋው ጭቁን ፣ ለወገኑ ብሎ፡፡

እንጂማ ቢል ኖሮ ፣ መጀመሪያ ራሴን፤
የምን ደሞ አገር ፣ ልጡር ደግ እናቴን፤
ለዚህ ያበቃኝን ፣ ምስኪኑን አባቴን፤...

ትምህርቱ ላይ ተግቶ ፣ ዲግሪውን ተሸክሞ፤
ማዕረግ በያይነቱ ፣ አጊጦ ተሸልሞ፤
"ከመኳንቱ" ጋር ፣ ሚኒስትር ተሹሞ፤
ንጉሱን አወድሶ ፣ ጎንበስ ለጥ ብሎ፤
ዶክተር ፕሮፌሰር ፣ ኖቤል ተቀብሎ፤
ሁልቆ መሳፍርቱን ፣ "ገሞራው!..." አስብሎ፤
መኖር ይችል ነበር ፣ በሀብት ተከልሎ፡፡

ግና...የሱ ማንነት ፣ ምድቡ ከትላልቆቹ፤
ገድሉና ታሪኩ ፣ ከሊቃውንቶቹ፤
ከመሲህዎቹ ጋር ፣ እንደሐዋርያቱ፤
ሆነ እጣ ፈንታው ፣ መከራን ማየቱ፤
ለእውነት ዘብ መቆም ፣ ለሌሎች መሞቱ፤
ቀድሞ እንዳለፉት ፣ እንደ ሰማእታቱ፡፡

በቡረቃው ዘመን ፣ በጎረምሳነቱ፤
ልጅ ያቦካው ለራት ፣ በሚተረትበቱ፤
ያ አይከሰሴውን ፣ የአጼውን ስርዓት፤
በድፍረት ሲታገል ፣ ለሀገሩ አርነት፤...

ቻይናንም ሲተቸው ፣ አስፈሪ ዘንዶውን፤
ምዕራቡንም ሳይቀር ፣ ብቸኛ ሀያሉን፤...

ወያኔን ሲያርደው ፣ በብዕር አለንጋው፤
ተገንጣይን ሲያወግዝ ፣ ከሀቅ ሲያጋጨው፤
ባንዶች ሲያዋርዱት ፣ ካገር ሲያሳድዱት፤
ባእዳንም ሲያግቱት ፣ አውቀው ሲያሳብዱት፤
ብቻውን ስቃዩን ፣ እንደተጋተረ፤
መንፈሰ ጠንካራ ፣ አርአያ ነበረ፡፡

ለኢትዮጵያ ፍቅሩ ፣ እንዲህ ሲብከነከን፤
ሲነድም ሲቃጠል ፣ ይህ ሁላ ዘመኑን፤
የሕዝቡ ሰቆቃ ፣ ነፍሱን ሲያስጨንቀው፤
ስደቱ ረሀቡ ፣ እረፍት ሲነሳው፤
ሲታመም ሲቃትት ፣ ሲሞተው... ሲሞተው...
እንደሻማ ቀልጦ ፣ ሳያርፍ አረፈ፤
ከእውነት ጋር ጸንቶ ፣ በእውነት አለፈ፡፡

ይብላኘ ለባእዳኖች ፣ ሀፍረት ለባንዳዎች፤
እሱ አንደው ተክቷል ፣ አዕላፍ ገሞራዎች፤
ያ ትውልድ ያለፈው ፣ ዛሬም በትግል ያለው፤
የሐዋርያው ፍሬ ፣ የባለቅኔው ዘር ነው፤
ገሞራው አይሞትም ፣ በነሱ ሕያው ነው፡፡

አገር ነጻ ሲሆን ፣ ወደፊት በትግል፤
ባንዳ ቦታ ሲለቅ ፣ ታሪክ ሲስተካከል፤
ጠቢብ የሚገባው ፣ ትውልድ ይመጣል፣
የዛኔ ገሞራው ፣ አክሊል ይቀዳጃል፡፡